Washington State Department of Commerce

RENT ASSISTANCE INFORMATION
OCTOBER 2021

# የ COVID-19 በኪራይ ላይ የሚሰጥ ድጋፍ አለ

የኪራይ መክፈያ ጊዜዎ ካለፈ ወይም ከኪራይ ቤት የመባረር አደጋ ላይ ከሆኑ፣ ሶስት አማራጮች አሉዎት።

- **የኪራይ ድጋፍ።** በመላ አገሪቱ የሚገኙ የአከባቢ ድርጅቶች የቤት ኪራይ ድጋፍን በማቅረብ ላይ ናቸው። እርስዎ ወይም አከራይዎ እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት በካውንቲዎ ውስጥ ያለውን የአከባቢውን ድርጅት ማነጋገር ይችላሉ።

  የኪራይ ድጋፍ አቅራቢዎች ዝርዝር፡- https://www.commerce.wa.gov/serving-communities/homelessness/eviction-rent-assistance-program/

  ዕድሜዎ ከ 25 ዓመት በታች ከሆነ ተከራይ ከሆኑ ፣ የአከባቢውን የ የወጣቶች እና የወጣት ጎልማሶች ከቤት ማስወጣት የኪራይ እርዳታ መርሃ ግብር አቅራቢን ያነጋግሩ። ዝርዝር፡- https://www.commerce.wa.gov/serving-communities/homelessness/youth-and-young-adult-eviction-rent-assistance-program/

- ከቤት የማስወጣት የመፍትሄ መርሃ ግብር። እርስዎ ወይም አከራይዎ በሚኖሩበት ካውንቲ ውስጥ በአከባቢዎ ያለውን የግጭት መፍቻ ማዕከልን ማነጋገር ይችላሉ። እነዚህ ማዕከላት ከቤት ማስወጣት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት ሊያግዙ ይችላሉ። ዝርዝር፡- resolutionwa.org/locations

- የሕግ አማካሪ የማግኘ መብት። የሕዝብ እርዳታን የሚቀበሉ ወይም በጣም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ተከራዮች -- ለአንድ ግለሰብ ዓመታዊ ገቢው $25,760 ወይም ለአራት ቤተሰብ $53,000 ከሆነ -- ከቤት የማስወጣት የፍርድ ሂደት አገልግሎት ከጠበቃ በነጻ ማግኘት ይችላሉ። ከቤት የማስወጣት መከላከያ ማጣሪያ በ 855-657-8387 የስልክ መስመር ይደውሉ ወይም ኦን ላይን ያመልክቱ፡- nwjustice.org/apply-online።

## የበለጠ ለማወቅ ከመንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይማሩ

Office of the Attorney General (የጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ) ጽሕፈት ቤት ስለነእነዚህ ፕሮግራሞች እና ሌሎች የአከራይ-ተከራይ ጉዳዮችን በተመለከተ በብዙ ቋንቋዎች ተጨማሪ የሕግ እና የፖሊሲ መረጃ በመስጠት ላይ ይገኛል፡- atg.wa.gov/landlord-tenant.

## ስለ ሌሎች ወጭዎች እርዳታ መረጃ ለማግኘት 2-1-1 ላይ ይደውሉ

እንደ የማብራት ክፍያዎች ፣ የምግብ ፣ የብሮድባንድ እና ሌሎችም ላሉት ነገሮች እንዲከፍሉ ለመርዳት መረጃ መስጠት ከሚችል ሰው ጋር ለመነጋገርwa211.orgን ይጎብኙ ወይም ለ 2-1-1 ይደውሉ።